# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ–ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 48 ነሀሴ 30/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገጾች


የክረምት በጎ ፍቃድ ሥራ አካል የሆነው የወጣቶች የሥነምግባር ማነቃቂያ ሥልጠና በቂርቆስ ክፍለ-ከተማ ተካሄደ
ገጽ 2

በብልሹ አሰራር የተሳተፉ 216 ሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰዱ ተገለጸ
ገጽ 3

“የ2018 በጀት ዓመት ጥንካሬዎቻችን ለማስቀጠል እና ውስንነቶቻችን ወደ 2019 በጀት ዓመት እንዳይሻገሩ ለማድርግ ጥራት ያለው እቅድ ተዘጋጅቶ ወደስራ ተገብቷል” ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ
ገጽ 5


**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካለዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ ባሉበት ሁነው ይጠቁሙ!**

## የዘርፎች የ2018 እቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና የ2019 በጀት ዓመት የዕቅድ ውይይት መድረክ ተካሄደ





የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የዘርፎችን የ2018 እቅድ አፈጻጸም እና የ2019 በጀት ዓመት እቅድ የውይይት መድረክ አካሄደ:: በውይይት መድረኩ ላይ የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮችና የስራ ኃላፊዎች ተገኝተው ከተሳታፊዎቹ ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል::

የኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ ለተሳታፊዎች ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፣ የየዘርፉ መከታተያ ክፍሎች ተልዕኮዎቻቸውን በብቃት ለመፈጸም የዘርፍ ፎረም አደረጃጀቶችን እንደ ትልቅ አቅም መጠቀም ይኖርባቸዋል:: የፎረም አደረጃጀት ጥሩ ውጤት እያመጣ ያለ እና ሦስቱንም የኮሚሽኑ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች ማለትም ማስተማር፣ መከላከል እና ህግ ማስከበርን በማስተሳሰር የሚተገብር መሆኑን አነስተዋል::

ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ዘርፎች ያሉበትን ቁመና ለመፈተሽ እድል የሰጠ ነበር ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በቀጣይ የ2019 በጀት ዓመቱም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን እና ሁሉንም ተቋማት ላይ ኮሚሽኑ መድረስ ስለማይችል



ልዩ ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው ጥቂት ተቋማት በስተቀር በዘርፍ ደረጃ ይካሄዳል ብለዋል:: ነገር ግን ዘርፎች ተቋሞቻቸውን በድጋፋዊ ሱፐርቪዥን መደገፍ ይገባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል:: ወርሃዊ የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ሪፖርትን በሚመለከት በየስድስት ወሩ እየተገመገመ ግብረ-መልስ እንደሚሰጥ ተናግረዋል::

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው 2018 በጀት ዓመት በሙስና መከላከል ጥናት፣

ወደ ገጽ 2 የዞረ

## በክልሉ ሙስናን በቁርጠኝነት መታገል እንደሚገባ ተገለጸ



የአማራ ክልል ከፍተኛ እና መካከለኛ መሪዎች የ2018 በጀት ዓመት ሥራዎች አፈጻጸም እና የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ ትውውቅ መድረክ ተካሂዷል:: በመድረኩ ላይ የተገኙት የክልሉ ርእሰ መሥተዳድር አረጋ ከበደ እንደገለጹት፤ በክልሉ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የሕዝብን መብትና ጥቅም ለማስከበር ብልሹ አሠራርን፣ ሙስናን እና ሌብነትን በጥብቅ መታገል ያስፈልጋል ብለዋል:: መሪዎችም በሁሉም የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎቻቸው ላይ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በቁርጠኝነት መታገል እንደሚገባቸው አሳስበዋል::

በተጨማሪም የክልሉን የገቢ አሰባሰብ አቅም ማሳደግ፣ የአገልግሎት ቅልጥፍናን ማሻሻል እና የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ማጠናቀቅ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለመገንባት ወሳኝ መሆናቸው ተገልጿል::

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት የጤና ቢሮ አመራሮችን ከኃላፊነታቸው ማገዱን ገለጸ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ጤና ቢሮ በፕሮግራም በጀት ተፈፅሟል በተባለ የንብረት ግዥ ዙሪያ የተነሳውን ጥያቄ ተከትሎ፣ የክልሉ መንግስት ጉዳዩን በምርመራ እንዲጣራ ማድረጉንና በጥርጣሬ ውስጥ የሚገኙ 3 አመራሮችን ከኃላፊነታቸው ማገዱን አስታውቋል::በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችና መገናኛ ብዙሃን በስፋት ሲነገር ከቆየው መረጃ በኋላ የክልሉ መንግስት ጉዳዩን በቅርበት ሲከታተል መቆየቱን ገልጿል:: የህዝብ ሀብት በአግባቡ፣ በቁጠባና ለታለመለት ዓላማ ብቻ ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የመንግስት ዋነኛ ኃላፊነት መሆኑን በመግለጽ፣ ከህዝብ የቀረበውን ጥቆማ በኃላፊነት ስሜት መቀበሉን አረጋግጧል::

ወደ ገጽ 3 የዞረ

# የክረምት በጎ ፍቃድ ሥራ አካል የሆነው የወጣቶች የሥነምግባር ማነቃቂያ ሥልጠና በቂርቆስ ክፍለ-ከተማ ተካሄደ





የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የክረምት በጎ ፍቃድ ሥራ አካል የሆነው የወጣቶች የሥነምግባር ማነቃቂያ ሥልጠና በቂርቆስ ክፍለ-ከተማ አካሂዷል:: በመድረኩ ላይ የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር እሸቴ አስፋው የተገኙ ሲሆን፣ የወጣቶችን አቅም በሥነምግባር መገንባት ለሀገር እድገትና ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ተናግረዋል:: ይህ ፕሮግራም የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት እና የወጣቶች ማነቃቃት እቅድ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር አካል ነው:: የሀገሪቱን የህዝብ ቁጥር 70 በመቶ የሚሸፍኑትን ወጣቶች በሥነ-ምግባር ማነጽ እና በሙስና መከላከል ስራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ማድረግ የተሻለች ሀገር ለመፍጠር ወሳኝ በመሆኑ የኮሚሽኑን ተልዕኮ ከወጣቶች ጋር በጋራ መስራት እንደሚገባ ኮሚሽነሩ ገልጸዋል::

የስልጠናው ዋና አላማ ዜጎች በሥነ-ምግባር ጎልብተው ሙስናን የሚጸየፉ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን፤ ወጣቶች ከስሜታዊነት ይልቅ ምክንያታዊነትን የሚያስቀድሙ፣ የሀላፊነትና የዜግነት ስሜት ያላቸው፣ ራስን የመግዛትና የበጎ ህሊና ባለቤት እንዲሆኑ ማሰልጠን እንደሚገባ ተሰምሮበታል::

በሌላ በኩል ከተሳታፊ ወጣቶች በኩል የሥነ-ምግባር ትምህርት ከትምህርት ቤት ጀምሮ ቢሰጥ፣ እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ያሉ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ለጥቆማ ምቹ አለመሆንን በተመለከተ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተዋል:: በተጨማሪም የጥቆማ ምስጢራዊነት ጥበቃ እና የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚገኙበትን ሁኔታ ክትትል ስራዎች ድንገተኛ ቢሆኑ የሚሉ ሀሳቦች ቀርበዋል::

ለተነሱት ጥያቄዎች አወያዮቹ በሰጡት ምላሽ፣ ወጣቶችን በሥነ-ምግባር የመገንባቱ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና የጥቆማ አሰራርን በተመለከተ ህብረተሰቡ የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብሄራዊ የሙስና መረጃ መጠቆሚያ ስርዓት (NCRS) መጠቀም እንደሚችልና ጥቆማዎችም ምስጢራዊነታቸው ተጠብቆ ተገቢው ክትትል እንደሚደረግባቸው ተገልጿል::



## የዘርፎች የ2018 እቅድ አፈጻጸም ግምገማ... ከገጽ 1 የዞረ

በሀብት ምዝገባ እና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ረገድ በርካታ ስራዎች የተሰሩበት እና ጥሩ ውጤት የተመዘገበበት ዓመት እንደነበር ገልጸዋል:: አክለውም በ2019 በጀት ዓመት እቅድ ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ "አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት" እንደ ሀገር እንዲተገበር ተግባብተናል ብለዋል::

ምክትል ኮሚሽነሩ አያይዘውም እቅዱን ውጤታማ ለማድረግ ተቋማት አሰራሮቻቸውን ማዘመን ይኖርባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል:: በፀረ-ሙስና ትግል ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ሀገራትን ተሞክሮ በመጥቀስ እንደ ሀገርም ዲጂታል መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ መጀመሩ አሰራርን የማዘመን አንዱ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል:: ይህም ህብረተሰቡ ይደርስበት የነበረውን እንግልትና የጊዜ ብክነት ያስቀረና እፎይታን ያስገኘ ነው ብለዋል::

የ2018 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን ያቀረቡት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ማስተባበሪያ መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ፈርዳ ገመዳ ዘርፎች በበጀት ዓመቱ ካከናወኗቸው ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ በአደረጃጀት፣ በድጋፋዊ ሱፐርቪዥን እና በፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ስራዎች ምን እንደሚመስሉ በሪፖርቱ አመላክተዋል:: በተለይ በወርሃዊ የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ስራዎች ላይ ከሪፖርት አቀራረብና ወቅቱን ጠብቆ ከመላክ አንጻር ውስንነቶች መኖራቸውን የቀረበው ሪፖርት አመላክቷል::

የመድረኩ ተሳታፊዎች ሪፖርቱ በበጀት ዓመቱ የነበሩ ጥንካሬዎችን እና ክፍተቶችን በትክክል ያሳየና ለቀጣይ ክፍተቶችን ለመዝጋት በትኩረት መስራት እንደሚጠበቅብን ያመላከተ ነው ብለዋል:: አያይዘውም ኮሚሽኑ ተግባርን ከመለካት አልፎ ውጤትን ወደ መለካት ተሸጋግሯል ያሉት ተሳታፊዎቹ፣ ለቀጣይ የምንሰራቸው



ስራዎች በምናከናውናቸው ተግባራት ሳይሆን በምናስመዘግባቸው ውጤቶች የምንመዘን ይሆናል ብለዋል:: ዘመኑ ሰው ሰራሽ አስተውሎትን መሰረት ያደረገ የሳይበር ጥቃት እየተበራከተ መምጣቱን እና ይህን ታሳቢ ያደረገ የፀረ-ሙስና ትግል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል::

በሌላ በኩል የቀረበው ሪፖርት የተጠቃለለ በመሆኑ ጥሩ የሰሩትን እና ያልሰሩትን ዘርፎችና ተቋማትን በግልጽ ለይቶ ለማወቅ አያስችልም፤ እንዲሁም አፈጻጸም ሪፖርት በዘርፍ ደረጃ መቀረቡ ውጤታማ ስራ የሰሩ ተጠሪ ተቋማትን የዋጠ ነው የሚል ሀሳብ በተሳታፊዎች ተነስቷል:: አያይዘውም ለወደፊት ጥሩ አፈጻጸም ያላቸውን ዘርፎችና ተቋማትን ለይቶ ማውጣትና ተሞክሮዎቻቸውን ማስፋት የሚቻልበት እድል ቢመቻች የሚል ምክረ-ሀሳብም አቅርበዋል::

በመቀጠል የ2019 በጀት ዓመት እቅድን የፀረ-ሙስና የህዝብ ግንዛቤ ማጎልበቻ ንቅናቄ ስራዎች ማስተባበሪያ መሪ ስራ አስፈጻሚ በሆኑት አቶ አለማየሁ ዘሪሁን አማካኝነት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል:: በውይይቱ ወቅትም እቅዱ ከአዋጁ ዋና አላማ ጋር የተዛመደ መሆኑን እና የመካከለኛ ዘመን የፀረ-ሙስና ትግል እቅድን ለማሳካት የሚያስችል መሆኑን ተሳታፊዎቹ ገልጸዋል:: ለዚህም ተግባር የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከወዲሁ የሥነ-ልቦና ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባቸው ተወያዮቹ አንስተዋል:: አያይዘውም ኮሚሽኑ



ለእቅዱ ፈጻሚዎች ተገቢውን ሙያዊ ስልጠና መስጠትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ሀሳብ ሰጥተዋል:: በተጨማሪም ለዘርፎችና ተቋማት የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ከ2019 በጀት ዓመት እቅድ ጋር የተገናኘ አጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሰጥቷል::

የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናው በዋናነት በሥራ ቦታ ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በውስጡም ከታማኝነት፣ ከምርታማነት፣ ከተግባቦት፣ ከጽናት፣ በጋራ ከመሥራት፣ ከቁርጠኝነት፣ ከገጽታ ግንባታ ወዘተ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ተዳስሰዋል::

የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናውን የሰጡት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ የኒላሸት ደሳለኝ፣ የ2019 በጀት ዓመት እቅድን ሥነ-ምግባርን በመላበስ እና በከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት መንፈስ ሆኖ ወደ ሥራ መግባት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል:: መሪ ሥራ አስፈጻሚው አያይዘውም በየተቋማቱ የሚስተዋሉ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ድርጊቶች እንዲታረሙ ለአመራሮች እና ሠራተኞች የሥራ ላይ ሥነ-ምግባር ሥልጠና መስጠት እንደሚያስፈልግ እና ይህንንም የማስተባበር ሥራ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው አሳስበዋል::

የሥልጠናው ተሳታፊዎች በበኩላቸው ከግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናው ብዙ እውቀት እንዳስጨበጣቸው እና በግንባር ቀደምነት ለመታገል የሞራል ትጥቅ እንደሆናቸው ገልጸዋል:: አያይዘውም የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ፍልስፍና ከውጭ የተቀዳ ሳይሆን በራሳችን የሥነ-ምግባር እሴቶች ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በጣም ጠቃሚ ነው ብለዋል:: በሥልጠና ሰነዱ ላይ የቀረቡ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግም አክለው ገልጸዋል::

በማጠቃለያ መድረኩ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት እና የሥራ አቅጣጫ የሰጡት ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ እንደገለጹት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናው ዋና ዓላማ ፈጻሚዎችን ለ2019 በጀት ዓመት እቅድ ተልዕኮ ለማዘጋጀትና የሥነ-ልቦና ትጥቅ ለማስታጠቅ ያለመ መሆኑን ተናግረዋል:: አያይዘውም ጥቂት ሙሰኞችን ከማሳደድ ይልቅ ተከታታይ ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን ማሳደግና አመለካከታቸውን መቀየር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል:: የሥነ-ምግባር ግንባታ ሥልጠናው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የገለጹት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በየደረጃው ያሉ መከታተያ ክፍል ሠራተኞች ሙያ ተኮር የሆነ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣቸዋል ብለዋል::

በመጨረሻም "ሌሎችን ለማስተማር እኛ የምንናገረውን ሆነን መገኘት ይኖርብናል" ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ ሥነ-ምግባርን በመገንባትና ሙስናን በመከላከል ረገድ ሁላችንም ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት ስላለብን ተግተን መስራት አለብን በማለት ማሳሰቢያ ሰጥተዋል::

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው፣ ሥነ-ምግባራዊ አሠራር እንዲኖር በሥነ-ምግባራዊ አመራርነት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል፤ ይህንንም የእቅዳችሁ አካል አድርጋችሁ መሥራት ይጠበቅባችኋል ብለዋል:: አክለውም የመከታተያ ክፍሎችን ሥራ ለመሥራት ሁለገብ እውቀት ያስፈልጋል፤ በተለይ በሙስና መከላከል ጥናት እና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት ሥራዎች የሚሠሩ ባለሙያዎች የተለያዩ ሕጎችን የሚያውቁና በሁሉም ሙያዎች የተካኑ እንዲሆኑ ሲሉ ገልጸዋል::

# በብልሹ አሰራር የተሳተፉ 216 ሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰዱ ተገለጸ

የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በዘርፉ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችና ህገ-ወጥ አሰራሮችን ለመግታት ባደረገው ርብርብ፣ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብልሹ አሰራር ውስጥ የተሳተፉ 216 ሠራተኞች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ መወሰዱን አስታወቀ።

ቢሮው ባለፉት ሁለት ዓመታት ያካሄደውን ተቋማዊ ሪፎርም በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ረገድ አበክሮ እየሰራ ይገኛል። በተለይም በተጠናቀቀው 2018 በጀት ዓመት ተሻሽሎ ስራ ላይ የዋለው ዲጂታል ሲስተም፣ ሂደቶችን በማሳጠር፣ ድግግሞሽን በማስቀረት እና አገልግሎቱን ፈጣን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ይህ ቴክኖሎጂ ደንበኞች በጊዜና በቦታ ሳይወሰኑ ቀልጣፋና ፍትሐዊ አገልግሎት በኦንላይን እንዲያገኙ ያስቻለ ሲሆን፣ በተቋሙ ውስጥ ተጠያቂነትን ለማስፈን ትልቅ አቅም ፈጥሯል።

ከቴክኖሎጂ ስርጭት ጎን ለጎን ህብረተሰቡን በክትትል ስራው ውስጥ ለማሳተፍ 7079 ነፃ የስልክ መስመር ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል። በዚህም በርካታ ደንበኞች በነፃ የስልክ መስመሩ አማካኝነት ጥቆማዎችን በመስጠት የሌብነት ተግባራትን ለመግታት ለሚደረገው ጥረት የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ ይገኛል። በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በየደረጃው የአሰራር ጥራት ኦዲት መካሄዱን፣ መመሪያና የአሰራር ጥሰት በተገኘባቸው ማህደራት ላይ የእርምት እርምጃዎች መወሰዳቸውን እና ባንክ የገቡ መሬቶች ላይም የኦዲት ቁጥጥርና ምርመራ መደረጉን ቢሮው ገልጿል።

የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች ከብልሹ አሰራር ነፃ ሆነው ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል፣ በዘርፉ ልምድ ባላቸው ምሁራን አማካኝነት ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፤ አሁንም እየተሰጡ ይገኛሉ። ሆኖም ከመንግስትና ከህዝብ የተሰጣቸውን አደራ ወደ ጎን በመተው የሥነ-ምግባር ግድፈት ያሳዩ ሠራተኞች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከደንበኞች በቀረቡ ጥቆማዎች እና በተደረገ የክትትል ስራ ህገ-ወጥ ተግባር ላይ የተገኙ 216 ሠራተኞች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የ6 ሠራተኞች የቅጥር ውል ሙሉ በሙሉ መቋረጡን ከቢሮው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ቢሮው በቀጣይም በየደረጃው ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና ህገ-ወጥ አሰራሮችን ለመከላከል የሚወስደውን ጥብቅ እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል።

# በትምህርት ዘርፍ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎች የ2018 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀምና በ2019 በጀት ዓመት እቅድ ላይ ግምገማዊ ውይይት ተካሄደ



የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የትምህርት ዘርፍ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎች የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ግምገማዊ ውይይት አካሂዷል። የግምገማዊ ውይይቱ ዓላማ በ2018 በጀት ዓመት በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተከናወኑ የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴዎችን፣ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን፣ የድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ረቂቅ ሪፖርትን እና የዕቅድ አፈፃፀሙን መገምገም፣ እንዲሁም የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ በመወያየት የቀጣይ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው።

በመድረኩ የኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው እንደገለጹት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር አምባሳደር ተማሪዎች የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን እንዲያግዙ በተገቢው መልኩ ተሳትፏቸውን ማጠናከር ይገባል። በተለይም የዩኒቨርሲቲ አመራሮች የፀረ-ሙስና ትግሉን በባለቤትነት የመምራት ኃላፊነታቸውን በተገቢው ሊወጡ እንደሚገባ አፅንዖት ሰጥተዋል። በቀጣይም በሦስቱ የፀረ-ሙስና ትግል ምሰሶዎች ማለትም በሥነምግባር ግንባታ፣ ቅድመ ሙስና መከላከልና ሕግ ማስከበር ሥራዎች ላይ በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመው፥ የሥራውን ውጤታማነት ለማሳደግ የተጀመረውን የድጋፍና ክትትል ሥራና ቅንጅታዊ አሠራርን ማስቀጠል እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው፣ ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ሥነምግባራዊ በማድረግ ብልሹ አሠራሮችን ማስወገድ ይገባል። የሚሰጡ የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠናዎችም በተቋማት የሚገኙ ክፍተቶችን በመለየት ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በቀጣይም ለሥነምግባር አምባሳደር ተማሪዎች ተገቢውን ሥልጠና በመስጠት፣ ብልሹ አሠራሮችን በመከላከል ላይ በትኩረት እንዲሠሩና ለፀረ-ሙስና ትግሉ አጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በግምገማዊ ውይይቱ የተሳተፉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎችም ሀሳብ፣ ጥያቄና





አስተያየቶችን አቅርበዋል። በተነሱት ጉዳዮችም ላይ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል።

# የሀረሪ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት የአገልግሎት ማሻሻያ የሚያደርጉ ውሳኔዎችን አጸደቀ

የሀረሪ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት (ካቢኔ) ያጸደቀው የ"ሀረሪ መሶብ" የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ድርጅታዊ መዋቅር በዋናነት የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በማስፈን ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትልቅ ሚና ይጫወታል በማለት ውሳኔ አሳልፏል።

ይህ ውሳኔ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ በማደራጀትና አሰራሩን ዘመናዊ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተገልጋዩንና የአገልግሎት ሰጪውን አካል የፊት ለፊት ግንኙነት በመቀነስ ለጉቦና ለህገ-ወጥ ክፍያዎች የሚከፈቱ ቀዳዳዎችን ይዘጋል። በተጨማሪም አሰራሩ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን መደረጉ አላስፈላጊ ቢሮክራሲያዊ እንግልትንና የደላሎችን ጣልቃ ገብነት ማስቀረት ያስችላል ተብሏል። በአጠቃላይ ዲጂታላይዝድ የተደረገው የአንድ ማዕከል አገልግሎት ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር በመፍጠር፣ ህዝቡ ላልተፈለገ ወጪ ሳይጋለጥ ፍትሃዊና ውጤታማ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ የሙስና ስጋቶችን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስ ተገልጽዋል።



## የደቡብ ምዕራብ... ከገጽ 1 የዞረ

ጉዳዩን ተከትሎ የፍትህ፣ የኦዲት እና የፀረ-ሙስና አካላት ተደራጅተው ወደ ምርመራ ስራ መግባታቸውን መንግስት አስታውቋል። ምርመራው በደረሰ ጥቆማና በአመራር ግምገማ መድረኮች በተነሱ ጭብጦች መነሻ፣ በጉዳዩ የተጠረጠሩ 3 አመራሮች ከኃላፊነታቸው እንዲታገዱ መደረጋቸውን ጠቁሟል።

የክልሉ መንግስት ማጣራቱና ምርመራው እንደተጠናቀቀ በሚገኘው ውጤት መሰረት፣ የህዝብና የመንግስትን ሀብት ባባከነ እና አግባብነት የጎደለው አሰራር በፈፀመ ማንኛውም አካል ላይ የማያዳግም ህጋዊ፣ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ርምጃ እንደሚወስድ በጽኑ አረጋግጧል። "የህዝብ ሀብት የህዝብ ነው፤ ማንም ከህግ በላይ ሊሆን አይችልም" ሲል የክልሉ መንግስት አክሏል።

በተጨማሪም የክልሉ መንግስት በመንግስትና በፕሮግራም በጀት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ ጠበቅ ያለ ክትትል የሚያደርግ መሆኑን ገልጿል። ጉዳዩን ሳጋለጠው ህዝብ ምስጋናውን ያቀረበ ሲሆን፣ ህዝቡ የነቃ ተሳትፎውን በማጠናከር እውነተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ብልሹ አሰራሮችን መጠቆምና ማጋለጡን እንዲቀጥል፣ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ተገቢውን መረጃ በመስጠት ትብብሩን እንዲያጠናክር ጥሪውን አቅርቧል።

# ፀረ-ሙስና


## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

ለህብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS


# ርዕሰ -አንቀፅ

## በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ሂደት ውስጥ መምህራን የማይተካ ሚና አላቸው!

አገርንና ዜጎችን ለከፋ ድህነት፣ ለኋላቀርነት እና ለጉስቁልና ከሚዳርጉ አስከፊ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ስር የሰደደ ሙስና ነው፡፡ ለሙስና መስፋፋት በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ የዜጎች የሥነ-ምግባር መጓደልና የሞራል ውድቀት ዋና መንስኤ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ለዕድገት ዕንቅፋትና ለሰው ልጆች ኢ-ፍትሐዊ አኗኗር መንስኤ የሆኑትን የሙስናና የብልሹ አሰራር ችግሮች በዘላቂነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በመልካም ሥነ-ምግባር የተገነባ፣ የመልካም ሥነ-ምግባር ግድፈቶችን፣ አድሎአዊ አሰራርንና ሙስናን የማይሸከም ትውልድ በትምህርት ተቋማት ውስጥ መገንባት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ወሳኝ ተግባር ነው፡፡

ከኋላቀርነት የተላቀቀችና የበለጸገች አገር ማየት የምንችለው ከአገራችን ጠቅላላ ሕዝብ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙትን ሕፃናትና ወጣቶች መልካም ሥነ-ምግባር እንዲኖራቸው፣ ሙስናና አድሏዊ አሰራርን እንዲጠየፉ እና ታማኝ እንዲሆኑ አድርገን በመቅረጽ አገር ተረካቢ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ሕፃናትና ወጣቶችን በመልካም ሥነ-ምግባር ቀርጾ የማውጣት ኃላፊነት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቢሆንም፣ በተለይም የትምህርት ተቋማት እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ትልቅ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸው በእውቀት፣ በክህሎት እና በቀና አስተሳሰብ በልፅገው እንዲወጡ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፤ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ደግሞ ተማሪዎችን ጨምሮ ዜጎች ሙስናን እንዲጠየፉ በመልካም ሥነ-ምግባር አስተምህሮ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ተቋም ነው፤ እየሰራም ይገኛል፡፡

የሰው ልጅ በእለት ተእለት የሕይወት ጉዞው ውስጥ በርካታ መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ እውቀቱንና ክህሎቱን እያዳበረ ይሄዳል፤ የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎቱ ሁልጊዜ የማያልቅና የሚጨምር በመሆኑ፣ ያለውን ተሰጥኦ ይበልጥ ለማዳበር ጥረት እያደረገ ትምህርትን በተለያየ መንገድ ይቀስማል፡፡ ትምህርት የሰው ልጅ ምክንያታዊና በሥነ-ምግባር የተገነባ ትውልድ ለመፍጠር ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ ምክንያታዊና በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፍና የሚታገል ሥነ-ምግባራዊ ማኅበረሰብን ለመፍጠር ያግዛል፡፡

በትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ሂደት ውስጥ መምህራን የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ መምህራን ራሳቸውን እንደ ሻማ አቅልጠው ለሌሎች ብርሃን የሚሰጡ የህብረተሰብ መሰቦች ናቸው፡፡ አዲስ የትምህርት ዘመን ሲበሰር ተማሪዎችን በእውቀት፣ በሥነ-ምግባርና በበጎ እሴቶች የመቅረፅ ታላቅ ኃላፊነታቸው እንደገና ይጀምራል፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱ፣ መምህራን ይህንን የማይተካ ሚናቸውን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በላቀ የቁርጠኝነትና የፍቅር ስሜት እንዲወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡



# ቆይታ

## “የ2018 በጀት ዓመት ጥንካሬዎቻችን ለማስቀጠል እና ውስንነቶቻችን ወደ 2019 በጀት ዓመት እንዳይሻገሩ ለማድረግ ጥራት ያለው እቅድ ተዘጋጅቶ ወደስራ ተገብቷል” ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ

**የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዲጂታል የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ስራዎችን በሰባት የተለያዩ አምዶች በመቃኘት በየ15 ቀኑ በዲጂታል ሚዲያ ለአንባቢያን ተደራሽ እያደረገች ትገኛለች፡፡ ከእነዚህ ሰባት አምዶች መካከል ቆይታ የሚለው ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዓምድ አማካኝነት የኮሚሽኑን የ2019 በጀት ዓመት የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ምን እንደሚመስሉ ለአንባቢያን ለማድረስ ከኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ ጋር አጭር ቆይታ አድርጋለች፡፡**



**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በመጀመሪያ ለቃለ-መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በፀረ-ሙስና ጋዜጣ ስም ከልብ አመሰግናለሁ፣ በመቀጠል ስምዎትን እና ኃላፊነትዎን ለአንባቢያን ያስተዋውቁልን?

**የእለቱ እንግዳ፡-** ስሜ አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ ይባላል በፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ነኝ፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ወደ 2019 በጀት ዓመት እቅድ ዝግጅት ከመሄዳችን በፊት በትውልድ የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ በ2018 በጀት ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎችና የተገኙ ውጤቶች እንዲሁም ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምን ምን ነበሩ? አጠር አድርገው ያብራሩልን?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** ዘርፉ በዋናነት ትውልድን በሥነ-ምግባር ኮትኩቶና አንጾ በማብቃት የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡና ሙስናን በመፀየፍ አምርሮ የሚታገል ዜጋን የመፍጠር እና ማህበረሰቡን የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት የማድረግ ዓላማን አንግቦ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት በ2018 በጀት ዓመት ከተከናወኑ የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ውጤት አመላካች ተግባራት(K-PI) መካከል ጥራት ያለው ስልጠና መስጠት አንዱ ነው፡፡ ስልጠናውን እውን ለማድረግ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት ያላቸው ምሁራንን በመመልመል ጥራት ያለውና ዘርፍ ተኮር የስልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በእነዚህ ምሁራን አማካኝነት የሀገሪቷ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ከሆነው የፓርላማ አባላት ጀምሮ በየደረጃው ላሉ የዘርፍና ተቋማት ሀላፊዎች ወይም አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠናውን መስጠት ተችሏል፡፡

ሌላው የዘርፍና ተቋማት መከታተያ ክፍሎችን በተለያዩ ስልጠናዎች አቅማቸውን ከመገንባት ባሻገር በየሩብ ዓመቱ ድጋፋዊ የሱፐርቪዥን ስራን በማከናወን የመደገፍና የማበረታታት ስራ ተሰርቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ ከተመዘገቡ ውጤቶች መካከል የተቋማት ሀላፊዎች የፀረ-ሙስና ትግሉን በባለቤትነት እንዲመሩት አስችሏል፡፡ ስለሆነም በየተቋማቱ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍና እየተሻሻለ መጥቷል፤ ለምሳሌ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ትልቁ ማሳያ ነው፡፡ እንዲሁም ዜጎች የጸረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆኑ በተሰራው የንቅናቄ ስራ ህብረተሰቡ ጥቆማ በመስጠትና ሙሰኞችን በማጋለጥ ረገድ ያለው ተሳትፎ እየጨመረ መጥቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙንን ተግዳሮቶች በሚመለከት፡- በራስ የውስጥ አቅም ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ብቃት ያለው የሰው ሀይል እጥረት እንዲሁም የምንሰጣቸውን ስልጠናዎች በመደበኛና በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የበጀት ውስንነት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ የ2019 በጀት ዓመት እቅድን ውጤታማ ለማድረግ ያከናወናቸውን የመጀመሪያ ምዕራፍ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን አጠር አድርገው ቢያብራሩልን?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** የ2019 በጀት ዓመት ዕቅድ የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን በተመለከተ የመጀመሪያው የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸሞቻችንን ገምግመን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይተናል፡፡ በመቀጠል ጥንካሬዎቻችንን ለማስቀጠል እና ውስንነቶቻችን ወደ 2019 በጀት ዓመት እንዳይሻገሩ ለማድረግ ጥራት ያለው የእቅድ ማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል፡፡ እቅዱም በኮሚሽኑ የማናጅመንት አባላትና ሰራተኞች፣ በዘርፍ ፎረም አመራሮች እና

በክልል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮች ተገምግሞና ጥልቅ ውይይት ተደርጎበት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

ፈጻሚውን አካል የማዘጋጀትና የማነሳሳት ተልዕኮ ሰጥቶ ወደስራ ለማሰማራት ዘርፎች ከዚህ እቅድ በመነሳት የራሳቸውን እቅድ አቅደው ወደ ተቋማት በማውረድ አራቱ የስራ ክፍሎች የጋራ እቅድ አዘጋጅተው ወደስራ እንዲገቡ አቅጣጫ ተቀምጧል። ከዚህም ጎን ለጎን ለዘርፍ ፎረም አመራሮችና የተቋማት መከታተያ ስራ አስፈጻሚዎች በእቅዱ የተመላከቱ ተግባራትን ለመፈጸም ያሉባቸውን ክፍተት መሙላት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በበጀት ዓመቱ ውጤታማ የሆነ የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ስራ ለማከናወን የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ምን ምን ናቸው? ከእነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎችስ ምን አይነት ውጤት ይጠበቃል?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** በ2019 በጀት ዓመት ልናከናውናቸው ከያዝናቸው ዋና ዋና የትውልድ ሥነ-ምግባር ግንባታ ስራዎች መካከል አንዱ የስልጠና ተደራሽነትን በማስፋት ብዛት ያላቸው ኃላፊዎች እና ሰራተኞችን ማሰልጠን ነው። ለዚህም ተግባር ዘርፍ ተኮር የሆነ ጥራት ያለውና ችግር ፈች የሆነ የሥልጠና ሞጁል ለማዘጋጀት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ስልጠናው ከአምናው በተለየ መልኩ በውስጥ አቅም የሚሰጥ ስለሆነ ከየዘርፉ የማሰልጠን ብቃት ያላቸው ሦስት ሦስት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሰራተኞችን በመመልመል የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጥቶ ወደ ስራ ለማሰማራት ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ሌላው በበጀት ዓመቱ የትኩረት ነጥብ ተብሎ የተያዘው የፈጻሚውን አቅም የማጎልበት ስራ ሲሆን፣ ከኮሚሽኑ ሰራተኞች ጀምሮ የተቋማት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ሰራተኞችን በስልጠና የማብቃትና ለተልዕኮ የማዘጋጀት ስራ በእቅድ ተይዟል። ከዚህ በተጨማሪም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመልካም ሥነ-ምግባራቸው የተሻሉና አርዓያ የሆኑ ተማሪዎችን የመለየት የሥነ-ምግባር አምባሳደር አድርጎ ተልዕኮ የመስጠት ስራን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ወደ ስራ ተገብቷል።

ከትግበራው በኋላ የሚጠበቀው ውጤት 1ኛ በአመለካከቱና በአስተሳሰቡ ራሱን የለወጠ ማህበረሰብ መፍጠር፣ 2ኛ የሙስናን አስከፊነት ጠንቅቀው የተረዱና ሙስናን በጽናት ለመታገል ቁርጠኛ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት፣ 3ኛ ሙስናን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ የዜጎችን ተሳትፎ ማሳደግ እና ሙሰኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** እነዚህን የትኩረት አቅጣጫዎች የሚመሩና የሚፈጽሙ የዘርፉ የስራ ክፍሎች ወይም ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው? የእያንዳንዱ የስራ ድርሻስ ምንድን ነው?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** እነዚህን ዋና ዋና ውጤት አመላካች ተግባራት የማስተባበር ሥራ የኮሚሽኑ እንዲሁም በዘርፉ ያሉ የስራ ክፍሎች ቢሆኑም የተቋማት ኃላፊዎች፣ የተቋማት አራቱ የስራ ክፍሎች ማለትም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ የህግ አገልግሎት፣ ለውጥና የውስጥ ኦዲትም የስራው ባለቤቶች ናቸው።

የስራ ድርሻቸውን ስንመለከት የኮሚሽኑና የዘርፉ የስራ ክፍሎች ሀገራዊ የትውልድ የሥነ-ምግባር ግንባታ ስራዎችን የማስተባበር፣ የመከታተልና የመደገፍ ስራዎችን ያከናውናሉ። የተቋማት ኃላፊዎች ደግሞ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በአግባቡ የመምራት፣ የማስተዳደርና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ሚናቸውን ይወጣሉ። የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሰጣቸውን ተልዕኮ ከመሰል የስራ ክፍሎች ጋር በመቀናጀት የፀረ-ሙስና ትግሉን ያስፈጽማሉ።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ከላይ ከተዘረዘሩት የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የስራው ባለቤት የሆኑ ሌሎች ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው? የስራ ግንኙነታቸውስ በምን ላይ ያተኩራል?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** የስራው ባለቤት ናቸው ብለን ከለየናቸው ባለድርሻ አካላት መካከል፣ የትምህርት ተቋማት ትውልድን በሥነ-ምግባር በማነጽ፤ የሃይማኖት ተቋማት ተከታዮቻቸው መልካም ሥብዕና እንዲላበሱ በማስተማር፤ የሚዲያ ተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎችን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለህዝቡ ተደራሽ የማድረግና አመለካከት የመቅረጽ፤ የሲቪክ ማህበራት ሀብት በማመንጨትና ሥነ-ምግባራዊ ትምህርቶችን በማስተማር ረገድ ጉልህ ድርሻ አላቸውና ከእነሱ ጋር ተቀራርቦ መስራትን ይጠይቃል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በእቅድ ትግበራው ወቅት ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ተግዳሮቶች ወይም ማነቆዎች ምን ምን ናቸው? እነሱንስ ለመሻገር ምን የተቀየሰ ስልት አለ?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** የበጀት ውስንነት በተለይ የምንሰጣቸውን ስልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በሚዲያ ለማስተላለፍ እጥረቱ ሊያጋጥም ይችላል። የባለሙያዎች የአቅም ውስንነት ሌላው ተግዳሮት ሊሆን ይችላል። የባለሙያዎች ከስራ መልቀቅ፣ ተቋማት ለመተባበር ፍላጎት አለመኖር፣ ችግሮችን በቁርጠኝነት የመጋፈጥ ቁርጠኝነት ማነስ የሚሉት በስጋትነት የተለዩ ናቸው።

እነዚህን ስጋቶች ለመሻገር የተቀየሱ ስልቶችን በሚመለከት፡- የውስጥ አቅምን ማጠናከር፣ ስልጠናዎችን በይነ-መረብ አማካኝነት መስጠት፣ የስራ ቦታን ሳቢና ምቹ ማድረግ፣ ከተቋማት ኃላፊዎች ጋር በመወያየት የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ፣ ጠቋሚዎች የህግ ከለላ እንዲገኙ በማድረግ ማበረታታት የሚሉት እንደ መፍትሄ ይወሰዳሉ።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ያላነሱት ወይም ቀረ የሚሉት ሀሳብ ካለ እንዲሁም ለአንባቢያን የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጠዎት?

**ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ ፈቃዱ ሰቦቃ፡-** ኢትዮጵያ የምትባል አንዲት የጋራ ሀገር አለችን፤ ይህችን የሁላችንም እናት የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ የማልማትና የማበልፀግ ሃላፊነት የሁሉም ዜጋ በመሆኑ የፀረ-ሙስና ትግሉ ያገባኛል በሚል እምነት ሙሰኞችን በማጋለጥ፣ መረጃ በመስጠት፣ በማስተማር ረገድ የህዝቡ ድጋፍና ትብብር እንዳይለየን በዚህ አጋጣሚ ጥሪየን ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

## አመሰግናለሁ!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የስክራፕ ብረት ሽያጭ ሂደት ላይ የቀረበ ጥቆማና የታዩ የአሰራር ክፍተቶች

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በብሔራዊ የሙስና መረጃ መቀበያ ስርዓት (NCRS) በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የቀረበው ጥቆማ፣ የሚወገዱ ስክራፕ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች ሽያጭ የግልፅ ጨረታ ሂደት ሕግ እና መመሪያውን የተከተለ አይደለም በሚል የቀረበን ጥቆማ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

የማጣራት ስራው፡- የፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ ቡድን በተቋሙ በአካል በመገኘት ከግዥ ክፍል ኃላፊና ከግዥ ኮሚቴ አባላት ጋር ውይይት በማድረግ፣ የግዥ ሂደቱን የሚያሳዩ ሰነዶችን በመመልከት እና መረጃ በመሰብሰብ የተካሄደ ነው፡፡

በማጣራት ሂደት የታዩ መረጃዎች፡ - ተጫራቾች ያስገቧቸው ሰነዶች፣ ጨረታው የወጣበት ሰነድ፣ የሽያጭ ውል ስምምነት ሰነድ፣ ጨረታው መሰረዙን የሚገልፅ ደብዳቤ፣ አሸናፊው ተጫራች ቅሬታ ያቀረበበት ማመልከቻ፣ ለቀረበው ቅሬታ ምላሽ የተሰጠበት ደብዳቤ፣ ተያያዥነት ያላቸው ደብዳቤዎች እና ቃለ-ጉባኤዎች፣ እንዲሁም የሽያጭ ጨረታ ሂደቱን የሚያሳዩ ክንውኖች ናቸው፡፡

የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የካቲት 07/2017 ዓ.ም ስክራፕ ብረታ ብረቶችንና አሉሚኒየም ባሉበት ቦታና ሁኔታ ለአቅላጭ ፋብሪካዎች ብቻ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ያወጣ መሆኑ፣ የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ ፕሮጀክት ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ስራ ክፍል ለኮሚዩኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ ጨረታው በማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲወጣለት በቀን 18/11/2017 ዓ.ም በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ የጠየቀ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ፕሮጀክት ፖርትፎሊዮ ማኔጅመንት በአዳሚ ቱሉና ሻሸመኔ ግምጃ ቤቶች አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን ስቲል ስክራፕ ብረቶች ሐምሌ 22/2017 ዓ.ም በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣ መሆኑ ታውቋል፡፡ አገልግሎት መስሪያ ቤቱ የማያገለግሉ ቁርጥራጭ ብረቶችን ለመሸጥ ሐምሌ 22/2017 ዓ.ም ያወጣው ጨረታ ለ15 ቀናት አየር ላይ ውሎ ከተዘጋ በኋላ በዚሁ ቀን በቀኑ ተከፍቷል፡፡

9 ተጫራቾች ማለትም ጋሻው አስቻለ፣ አደም ናስር፣ ጎሳዩ ገቢ፣ ሃሺም አሊ፣ የትንቢ ትሬዲንግ፣ ናትናኤል ሰለሞን፣ ነጋ ኑርዬ፣ አሸናፊ ይርዳው እና ተሾመ ገዷአ የተባሉት ተጫራቾች ጨረታው ላይ ተመዝግበዋል፡ ፡ ከቀረቡት 9 ተጫራቾች ውስጥ ስምንቱ (8) ተጫራቾች ባቀረቡት አነስተኛ ዋጋ ምክንያት ያላለፉ ሲሆን፣ የተወዳደሩት ዘጠኙም (9) ተጫራቾች አገልግሎት መስሪያ ቤቱ ቁርጥራጭ ብረቶችን ለማስወገድ በሚል ባወጣው ጨረታ ማስታወቂያ ተወዳድረው የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ ናቸው፡፡

ከተወዳደሩት 9 ተጫራቾች ውስጥ አገልግሎት መስሪያ ቤቱ ባወጣው ጨረታ መሰረት ጋሻው አስቻለ የተባለ ተጫራች ባቀረበው ከፍተኛ ዋጋ ጨረታውን ያሸነፈ ሲሆን፣ የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የማያገለግሉ ንብረቶች ሽያጭ አፅዳቂ ኮሚቴ በሻሸመኔ ከተማ የሚገኙ ብዛታቸው በግምት 183,451 ኪ.ግ የሆኑ ስቲል ስክራፕ ብረቶች ለጨረታ ቀርበው አቶ ጋሻው አስቻለ ባቀረቡት ለአንድ ኪ.ግ ዋጋ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ብር 107.29 አሸናፊ እንደሆኑ ገልጿል፡፡ በአጠቃላይ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ 19,682,457.79 ብር አሸናፊ ስለሆኑ ሽያጩ እንዲፀድቅ እና በርክክብ ወቅት ከተጠቀሰው መጠን በላይ ብዛት ቢገኝ አሸናፊው ተጫራች በአሸነፈበት ዋጋ ለመውሰድ ፈቃደኛ መሆኑ ተጠይቆ እንዲሸጥለት የሚል ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

የንብረት አስወጋጅ/ሽያጭ ግምገማ ኮሚቴ፣ ጋሻው አስቻለ ባቀረበው አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ስቲል ስክራፕ ብረቶች መግዣ ነጠላ ዋጋ ብር 93.29565 ግምታዊ ክብደት መጠን 183,451.00 ኪሎ ግራም በጠቅላላ ቫትን ጨምሮ በ19,682,457.79 ብር ያሸነፈ በመሆኑ፣ ከአገልግሎት መስሪያ ቤቱ ጋር ውል ገብቶ የሽያጭ ሂደቱ እንዲከናወን ይወስናል፡፡

የንብረት ሽያጭ/አስወጋጅ አፅዳቂ ኮሚቴ ለአገልግሎት መስሪያ ቤቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በላከው የውስጥ ማስታወሻ በሽያጭ ጨረታ ቁጥር EEU/PPM/NCB/02/2018 መሰረት በሻሸመኔ (በሎቶ-2) ለሽያጭ የቀረበውን 183,451 ኪሎ ግራም የሚወገድ ቁርጥራጭ ብረት አሸናፊው ባቀረበው የአንድ ኪሎ ግራም ከፍተኛ ዋጋ ቫትን ጨምሮ በብር 107.29 ተባዝቶ በብር 19,682,457.79 ጨረታውን ካሸነፈው ተጫራች ከጋሻው አስቻለ ጋር በጨረታ ሰነዱ መሰረት ውል ታስሮ ሽያጩ እንዲከናወን በማለት ይወስናል፡፡

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በቀን 09/10/2017 ዓ.ም በቁጥር 02/35/2921 በፃፈው ደብዳቤ፣ የአሰራር ሂደቶችን በመከተል ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጣቸውን ማስረጃ ታሳቢ ያደረገ በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል ብቻ በገበያ ዋጋ በማወዳደርና በመሸጥ ሀገራዊ ችግሮችን የማቃለል ሚናችሁን እንድትወጡ የሚል ጥሪ አቅርቦ ነበር፡፡

ነገር ግን ከአገልግሎት መስሪያ ቤቱ በቀን 07/02/2018 ዓ.ም በቁጥር 11-12/ፕ.ፖ.ማ/240 በተፃፈ ደብዳቤ ምክንያቱ ሳይገለፅ ጨረታው ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ መሆኑ ታውቋል፡፡ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለአገልግሎት መስሪያ ቤቱ በቀን 17/02/2018 ዓ.ም በቁጥር 02/35/3106 በተፃፈ ደብዳቤ ሴንቲኔል ስቲል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለውን አቅላጭ ኢንዱስትሪ ብቻ መርጦ በመላክ፣ በሁለቱም መጋዘኖች ማለትም በአዳሚ ቱሉ 17,600 ኪሎ ግራም የሚመዝን ለአንድ ኪሎ ግራም ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር 114.50 እና በሻሸመኔ 183,451 ኪሎ ግራም የሚመዝን ለአንድ ኪሎግራም ዋጋ ቫትን ጨምሮ ብር 93.29565 የሚያክል ግምት ያላቸው ቁርጥራጭ ብረቶች እንዲተላለፋለት በማለት ደብዳቤ ይጽፋል፡፡ አገልግሎት መስሪያ ቤቱም ከሴንቲኔል ስቲል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር የሚወገዱ ስክራፕ ብረታ ብረቶችን ለመሸጥ ይዋዋላል፡፡

የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች፡- የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ ያወጣው የሚወገዱ ስክራፕ ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች ሽያጭ የግልፅ ጨረታ ሂደቱን ጠብቆ እየተጠናቀቀ እያለ በቁጥር 11-12/ፕፖማ/240 በቀን 07/02/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መቋረጡ የተገለፀ ቢሆንም የተቋረጠበት ምክንያት አለመገለፁ፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ቁርጥራጭ ብረታ ብረቱ ከዘርፉ ማህበር ጋር ፍላጎትን መሰረት በማድረግ ለሴንቲኔል ስቲል ኃ/የተ/የግ/ማህበር በወቅቱ በቀረበው ከፍተኛ ዋጋ እንዲተላለፍለት የለየበት መስፈርት በተገቢው ያልተገለፀ መሆኑ ናቸው፡፡

ምክረ-ሐሳብ፡- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ (EIH) መስከረም 06/2018 ዓ.ም በቁጥር EIH/01/0010/18 በተጻፈ ደብዳቤ አምራቾች ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል ብቻ በሚደረግ ውድድር እንዲሸጡ ስለሚጠይቅ፣ ከዘርፉ ማህበር ጋር በመመካከርና ፍላጎትን መሰረት በማድረግ የአርማታ ብረት አምራች ለሆነው ሴንቲኔል ስቲል ኃ/የተ/የግ/ማህበር በወቅቱ ባቀረበው ከፍተኛ ዋጋ እንዲተላለፍለት ተለይቶ መቅረቡን በቀን 17/02/2018 ዓ.ም በቁጥር 02/35/3106 ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ስለሆነም የውጭ ምንዛሬን ከማስቀረት አኳያ፣ እንዲሁም የገንዘብ ሚኒስቴር ቅድሚያ ለአቅላጭ ኢንዱስትሪዎች ከተቀመጠው አነስተኛ ዋጋ በላይ አወዳድሮ መስጠት በሚለው መመሪያ መሰረት ሽያጩ ውል ለተገባው ለሴንቲኔል ስቲል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ቢሸጥ የሚል ምክረ-ሐሳብ እናቀርባለን፡፡

ይህን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት በዚህ አምዳችን ስናቀርብ፣ ሌሎች ተቋማት ሙስና ከመከሰቱ በፊት እንዲማሩበት በማሰብ ነው፡፡

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

”የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት በየጊዜው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል:: ከእነዚህም መድረኮች መካከል በየሁለት ሳምንቱ ለንባብ የሚበቃው ዲጂታል ጋዜጣችን አንዱና ዋነኛው ነው:: ጋዜጣችን ከያዛቸው አበይት ዓምዶች መካከል ‘ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር’ የሚለው ይገኝበታል:: በዚሁ መሠረት በዚህ እትማችን ለህብረተሰቡ ትምህርት ይሰጣሉ ብለን ያመንንባቸውንና በሙስና ወንጀል የተሳተፉ ግለሰቦችን ጉዳይ አስመልክቶ የተዘጋጀውን ዝርዝር መረጃ ለአንባቢዎቻችን አቅርበናል::”

ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጅ የነበረ ግለሰብ ክስ ተመሰረተበት

ተከሳሽ ካሊድ አወል የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ልዩ ቦታው አዲሱ ገበያ ከሚገኝ አንድ የገበያ ማዕከል ውስጥ ነው:: የጉለሌ ክ/ከተማ ፖሊስ ዋና መምሪያ ኢንተለጀንስ ለተከታታይ ሦስት ቀናት ባደረገው ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ካሊድ አወል የተባለ ግለሰብ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን እንደሚያዘጋጅ አረጋግጧል::

ግለሰቡ በዋና መምሪያው ኢንተለጀንስና ኦፕሬሽን በቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ ከተያዘ በገበያ ማዕከሉ ውስጥ በሚገኘው የህትመት ስራ በሚያከናውንበት የንግድ ቤት ውስጥ በተደረገ ብርበራም በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ስም የተዘጋጁ ሀሰተኛ ሰነዶች ተገኝተዋል:: ከተያዙት ውስጥም የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ወሳኝ ኩነት፣ የቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ወሳኝ ኩነት፣ የየካ ክ/ ከተማ ሰነዶች ማረጋገጫ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጣቢያ ፅ/ቤት የራስጌና ክብ ማህተም፣ የልደት የምስክር ወረቀት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ስለ ግብር አከፋፈል የሚሰጥ ማስረጃ ፣የፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ የፎረንሲክ ማስረጃ፣ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ማስረጃ እንዲሁም ሀሰተኛ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚጠቀምባቸውን 2 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር፣ ፍላሾችና ፕሪንተር ይገኙበታል::

ፖሊስ በማስረጃ የተጠናቀረውን የምርመራ መዝገብ ለክፍሉ ዐ/ህግ በመላክ ክስ እንዲመሰረትበትም አድርጓል::

ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትም ሆነ ማሰራጨት በሀገር ምጣኔ ሀብትና ደህንነት ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በተጨማሪ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ህብረተሰቡ በመረዳት በመሰል ድርጊት ውስጥ የሚገቡ ግለሰቦችን ለህግ አሳልፎ መስጠት እንደሚገባም የአዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ መልዕክቱን አስተላልፏል::

ወደ ሌላ የውሳኔ ዜና ስናልፍ የቻይናው የንብረት ግዙፍ ኩባንያ ኤቨርግራንዴ የቀድሞ ሊቀመንበር ሹ ጂያይን በከባድ የገንዘብ ማጭበርበርና የሙስና ወንጀሎች ጥፋተኛ በመሆናቸው የእድሜ ልክ እስራት ተፈረደባቸው::

የሼንዘን መካከለኛ የሕዝብ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ፣ የሹ ጂያይን የግል ንብረታቸው በሙሉ እንዲወረስ እና የፖለቲካ መብታቸውን በእድሜ ልክ እንዲነጠቅ፤ ከወንጀል የተገኙ ሕገወጥ ገቢዎች እንዲመለሱ እና ጉድለት ካለ እንዲሟላ ትዕዛዝ ሰጥቷል:: ፍርድ ቤቱ እንዳረጋገጠው፣ ሹ ጂያይንና እሳቸው የሚመሯቸው ኩባንያዎች የፋይናንስ ሪፖርቶችን በማጭበርበር፣ የንብረት ዋጋን በማጋነን፣ ዕዳዎችን በመደበቅ እና የገንዘብ ተቋማትን ለመቆጣጠር ጉቦ በመስጠት ተጠቃሚ ሆነዋል::

እነዚህ ድርጊቶች የኩባንያውን የፋይናንስ ችግር ከማባባስ በተጨማሪ ባለሀብቶችን፣ ተቋማትንና ሕዝብን ከፍተኛ ኪሳራ እንዲያጋጥማቸው አድርጓል ተብሏል:: በጉዳዩ ላይ ኤቨርግራንዴ ግሩፕና የሪል እስቴት ክፍሉ በድምሩ 15.82 ቢሊዮን ዩዋን ቅጣት ተጥሎባቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች 56 ተከሳሾች ከ1 ዓመት ከ10 ወር እስከ 18 ዓመት የሚደርስ እስራት ተፈርዶባቸዋል:: የኤቨርግራንዴ ጉዳይ በአንድ ትልቅ ኩባንያ ውስጥ ከፍተኛ ሙስና፣ ሥልጣንን አላግባብ መጠቀምና የፋይናንስ ማጭበርበር በአንድ ላይ ሲጣመሩ ምን ያህል ከባድ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ ሆኗል ተብሏል:: ቻይና ዴይሊ እንደዘገበው፣ የሹ ጂያይን ጉዳይ ከፍተኛ ሥልጣንና ሀብት ከሕግ በላይ እንዳልሆነ የሚያስጠነቅቅ ጠንካራ መልዕክት እንደሆነ ተመላክቷል::

# መልካም ዜጋ

## የታማኝነት ተምሳሌታዊ ተግባር

ወጣት ስጦታ ወ/የሱስ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጠምባሮ ልዩ ወረዳ የሙዱላ ከተማ ነዋሪ በስህተት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ቅርንጫፍ ወደ ንግድ ባንክ አካውንቱ የገባውን 300,000 (ሶስት መቶ ሺ.ህ) ብር በታማኝነት ለባለቤቱ ተመላሽ አድርጓል::


ወጣት ስጦታ እንደገለፀው ብሩ ወደ ንግድ ባንክ አካውንቱ ከማያቀው ሌላ አካውንት መግባቱን እንዳረጋገጠ በተለያዩ የአካባቢው ሚዲያዎች የገንዘቡ ባለቤት ተዓማኒነት ባለው አካውንቱ ሲልክለት ተመላሽ እንደሚያደርግ አጭር ቪድዮ በመስራትና በጽሑፍ መረጃዎችን ከማዳረስ ባሻገር ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነፃ የስልክ መስመር 951 ደውሎ አሳውቋል::


በዚሁ መሠረት ብሩ ሙሉነሽ ኦሌቦ ከተሰኘች ግለሰብ ከሀዋሳ ንግድ ባንክ ታቦር ቅርንጫፍ በስህተት የተላከ መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው 300,000(ሶስት መቶ ሺ. ብር) ለባለቤቷ ተመላሽ ያደረገው::

የጠምባሮ ልዩ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ዋና ኢንስፔክተር ኃይሉ ደፋር እንደተናገሩት ወጣት ስጦታ ወ/የሱስ የሰው ገንዘብ እንደማይጠቀም በመገንዘብ በታማኝነት ለባለቤቱ








እንደመለሰ በመጠቀም ወጣቱ ላደረገው በጎ ተግባር አመስግነዋል:: ሌሎች ወጣቶችም የወጣት ስጦታ ወ/የሱስን ዓይነት ተሞክሮ በመቀበል የራስ ነገር ያልሆነ ማንኛውም ነገር የማይጠቅም መሆኑን በመረዳት ታማኝ ሊሆኑ እንደሚገባና በዚህ የገንዘብ ፍቅር በበዛበት ዘመን እንደ ስጦታ ያሉ ታማኝና የመልካም ግብረ ገብነት ባለቤት መሆን የህሊና እረፍትን የሚሰጥ እንደመሆኑ ወጣቱ ትውልድ ይህን መልካም ተሞክሮ ሊወስድ እንደሚገባ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል:: መልካምነት ሁልጊዜም ለራስ ነውም ብለዋል በመልዕክታቸው::

የወጣት ስጦታ ተግባር ሥነ-ምግባር ከህግ በላይ የግል ምርጫ እና የውስጥ እሴት መሆኑን ያስረዳል:: በስህተት የገባ ገንዘብን መያዝ በራሱ በህግ ወንጀል ተደርጎ ባይቆጠርም እንኳ (እስከተወሰነ ገደብ ድረስ) የግለሰቡን ታማኝነት እና የህሊና ንጽህና የሚፈትን ወሳኝ ወቅት ነው:: ማንም ሳያየው፣ ምንም ተጠያቂነት ሳይኖርበት፣ ትክክለኛውን ነገር መምረጡ የስነ-ምግባር እውነተኛ መገለጫ ነው::

ይህ ተግባር ከሙስና እና ከገንዘብ ብልሹ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ሰፊ ትምህርት ይሰጣል፡ ሙስና የሚጀምረው ብዙውን ጊዜ “የራስ ያልሆነን ነገር በአጋጣሚ ማግኘት” ከሚል ትንሽ ውሳኔ ነው:: ወጣት ስጦታ እንዳሳየው ግን፣ ታማኝነት ልማድ ተደርጎ ሲወሰድ በትንንሽ አጋጣሚዎች ውስጥ ራሱን ያሳያል:: ይህም ወደ ትልቅ ማህበራዊ አመኔታ እና ንጹህ ተቋማዊ ባህል ይመራል::

ለወጣቱ ትውልድ የሚተላለፈው መልእክት ግልጽ ነው:: ሥነ-ምግባር ማለት በትልቅ ውሳኔዎች ብቻ ሳይሆን በዕለታዊ፣ ትንንሽ በሚመስሉ ምርጫዎች ውስጥ የሚገለጽ የህይወት አቋም ነው:: እንደዚህ ያሉ ተሞክሮዎችን ማስተዋወቅ እና ማበረታታት ደግሞ ሰፊውን የፀረ-ሙስና ትግል ከህግ ማስከበር ባለፈ ወደ ማህበረሰባዊ እሴት የመቀየር ስራ አካል ነው::



# ኪነ-ጥበብ

## ስግብግብ ነጋዴ!

ሚዛኑን አጉድሎ ትርፍ የሚያሳድደው፣
የድሀውን ኑሮ እጅግ ያከብደው፣
ከህዝቡ ጉረሮ ነጥቆ የሚበላው፣
በጥቅም ተሳስሮ ከባለስልጣኑ ከዚያም ከደላላው::
ሙሰኛው ነጋዴ የገበያው አውሬ፣
ነገን ማየት ትቶ የሚኖር ለዛሬ::
ጨምሮ እየሸጠ አፈር ከበርበሬ::
እህልን ደብቆ በመጋዘን ውስጥ፣
ዋጋውን በመስቅል ለድሀው የሚሸጥ፣
ህጻናት ተርበው እሱ ሊለወጥ::
የህዝብ መከራ የትርፉ ምንጭ ነው፣
የወገኑ እንባ የኪሱ መሙያ ነው፣
ሙሰኛው ነጋዴ የሀገር ባንዳ ነው::
ሙሰኛው አመራር በጥቅም ያበደ፣
ለመዝረፍ የሚያመች ህግ እያወረደ፣
እስከመቸ ሊኖር ብልጥ እየነገደ፣
ህሊና ተሸጦ ሆድ እየፈረደ::
ብርን እያመለክ ርህራሄ ርቆህ፣
እምነት ተስፋ ፍቅር ጠፍቶ ከህሊናህ፣
ለስጋ የምትኖር የሰማዩን ትተህ፣
እስከመቼ ትኖር ከእውነት ተጣልተህ::
ሀብቱን ያከማቻል ቀኑን ሳያውቀው፣
በድንገት ሲጠራ ላይከተለው፣
የሚለው ሥነ-ቃል የተነገረው፣
ከቶ ላንተ ነበር ብታስተውለው::
ስለዚህ ተመለስ ከክፉው መንገድህ፣
እውነትና ፍትህ ይሁን መመሪያህ፣
የሰው ምርቃት ነው ሀብትን የሚያስቀጥል፣
የሀሰት ትርፍማ ገደል ነው የሚጥል፣
ስጋም ከሞት አይድን ነፍስም ከመቃጠል::